# ኢትዮጵያ በሽግግር ወቅት ላይ

**Rout Tsega/Germany**

ላለፉት 22 አመታት ኢትዮጵያን በመግዛት ላይ የሚገኘው የህወሓት መንግሥት ተቃዋሚዎችን በመግደል በማሰርና በማሳደድ ስልጣኑን እያራዘመ ይገኛል።ሆኖም በአሁኑ ግዜ ተቃውሞ እየበረከተ መጥቷል። በቅርቡ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ህዝብ በአዲስ አበባ እና በሌሎችም ከተሞች ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍ አድርጓል።ለማድረግም በዝግጅት ላይ ይገኛል።

ባለፈው በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት በተካሄዱት ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፎች ከ 200 በላይ ሰዎች ተገለዋል። በዚህ መሰረት ለተወሰኑ አመታት ህዝባዊ ተቃውሞ በረድ ብሎ ነበር። አሁን ግን ቀንደኛው መሪ አቶ መለስ ዜናዊ ይሄን አለም ከተሰናበቱ ወዲህ ገዢው ፓርቲ እርስ በርሱ ባለመተማመንና አቶ መለስን የሚተካ ሰው ባለማግኘታቸው በስልጣን ሽሚያ ላይ ናቸው። ሀገሪቱን ለስሙ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ እመራለሁ ቢሉም አገሪቱ በሞተ ሰው በመለስ ዜናዊ ራእይ (ቅዠት) በመመራት ላይ ትገኛለች።

አገሪቷን እመራለሁ የሚለው የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት በአሁኑም ግዜ ይህንኑ መጠሪያ ካለመቀየሩም በላይ ምን እንደሆነ ባልታወቀ ርእዮተ አለም አገሪቱን በመምራት ላይ ይገኛል። አመጣጣቸው የአልባንያን አይነት የኮሚኒስት ሥርዓት ለመመስረት ነበር። ነገር ግን በጊዜው የቀዝቃዛው ጦርነት በመውደቁ ባያምኑበትም ከምዕራባውያኑ ሊገኝ የሚችለውን እርዳታ በማሰብ የካፒታሊስቱን ሥርዓት እንከተላለን ቢሉም ነገር ግን ሶሻሊዝም በማካሄድ መሬትን በመከፋፈል የመንግስት በማድረግ የራሳቸውን የጎሳ ፖለቲካ በማስፋፋት ሌላውን ህዝብ ተመልካች ከማድረጋቸውምበላይ የቀድሞ መንግሥታዊ ድርጅቶችን በማፈራረስ በዘር ላይ የተመረኮዘ ወታደራዊ ፖሊሲ አስተዳደር ለመመሥረት ደፋ ቀና እያሉ ናቸው።

ከውጭ የሚገኘው ዕርዳታ እንዳይቋረጥ በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች የተከበሩ ለማስመሰል ብቻ ከወረቀት መዝለል ያልቻለ ሕገ-መንግስት በማርቀቅ አስመሳይ ተግባራትን ከማከናወን ይልቅ ለህዝቡ ጠብ የሚል ስራ መስራት አቅቶት በመዳከር ላይ ያለ ስርዓት ነው የወያኔ ስርዓት። በአገሪቱ ሃሳብን በነፃ የመግለጽ መብት ተነፍጎ ዜጎች የመሰላቸውን ለመጻፍና ለመናገር የግድ ወደ ሶስተኛ አገር መሰደድ ግድ እንዲላቸው እየተደረገ ነው። የመንግስት መገናኛ ብዙሃንም ለስርዓቱ ፕሮፓጋንዳ መሳሪያ በመሆን የፈጠራ ወሬ ጭምር በማስተጋባት ህዝቡ ሌሎች ሚዲያዎችን እንዳይከታተል ጭምር አፈና እየተደረገበት ይገኛል። ይሄ አፈና በተለይ በአረቡ ዓለምና በሰሜን አፍሪካ ህዝባዊ አመጾች የመንግስት ለውጥ በማስከተላቸው የወያኔ ስርዓትን ፍርሃት አጠናክሮታል።

በመከራ ውስጥ ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለይምሰል በአገር ውስጥ ቢንቀሳቀሱም በወያኔ ደህንነቶችና ፖሊሶች እጅ ተወርች ታስረው ከፍተኛ ማሳደድና ማስፈራራት እየደረሰባቸው ስራቸውን ባግባቡ እንዳይወጡ ተደርገዋል።እንዲሁም ከህዝብ ጋር እንዳይገናኙ በመደረግ ላይ ናቸው።

የምእራቡን ዓለም ግን በሐሰተኛ የስታቲስቲክስ መግለጫ በማወናበድ በሀገሪቱ ላይ ዲሞክራሲ ያለ በማስመሰል ርካሽ ህንጻዎችን በመገንባት ዓመት የማይቆዩ መንገዶችን ሠራን በማለት እንዲሁም ለስሙ ዩኒቨርሲቲዎች አስፋፋን በማለት ያለ አስተማሪ ያለ መጽሐፍ ያለ ላብራቶሪ እና የመሳሰሉትን መሳሪያዎችን ሳያሟሉ ከተመረቁም በኋላ ሥራ ያለማግኘት ችግሮች እየተስተዋሉ ናቸው።ስራ ለማግኘትም የገዢው ፓርቲ አባል መሆን እንደ አንድ ድብቅ መስፈርት ከሆነ ውሎ አድሯል።አለበለዚያም ያላቸው ምርጫ ወደ ስደት መሄድ ነው።

ባሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የፈለገው መጠሪያ ይሰጠው ህዝቡ ፍራቻውን በመተው በሰላማዊ ሰልፍ ብሶቱን በማስተጋባት ላይ ይገኛል። በቅርቡ በደሴ በጎንደር በባህር ዳር በጂንካ በአርባ ምንጭ በወላይታ በሶዶ ወዘተ ህዝባችን በብዛት ወጥቶ ብሶቱን በማሰማት ላይ ከመገኘቱም በላይ ገዥው መደብ ለምዕራቡ ዓለም ሀገሪቱን ሽብርተኝነት እያሰጋት ነው በማለት ጥፋት የሌላቸውን ጋዜጠኞችንና የተቃዋሚ ፖለቲከኞችን በራሱ ፍርድ ቤት በራሱ ዳኞች ከ18 ዓመት እስከ እድሜ ልክ በማሰርና በማንገላታት ላይ ይገኛል።

ስለሆነም እንደ ጀርመን ያሉ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ድጋፍ በመስጠት ላይ ያሉ አገራት እርዳታቸው በትክክል ስራ ላይ ስለማዋሉና በአገሪቱ ሰብዓዊ መብቶች ስለመከበራቸው ማረጋገጫ ሳያገኙ ድጋፋቸውን እንዳይቀጥሉ ምርመራ ሊያደርጉ ይገባቸዋል። የሰለጠኑት አገሮች ለእያንዳንዱ ህዝባቸው መብት መከበር እንደሚጨነቁትና ስደተኞችንም ጭምር በመርዳት ሙሉ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ሁሉ የህዝባችንን እንባ ለማበስ የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። በውጭም ይሁን በአገር ውስጥ የምንገኝ ኢትዮጵያውያንም ለነፃነታችን የምናደርገውን ማናቸውንም ትግል አጠናክረን መቀጠል እንደሚገባን ማሳሰብ እፈልጋለሁ። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይጠብቅልን!

**ጥላ መጽሔት/ tilamagazine.yolasite.com**
**September 19/2013**